## ትምህርት 14

1. አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ካሉ በኋላ ምን አደረጉ?

ሀ- ለራሳቸው የቅጠል ልብስ ሰሩ።

2. አዳምና ሔዋን ለራሳቸው የቅጠል ልብስ የሰሩት ለምንድን ነው?

ሀ- ኃጢአታቸውን ለመደበቅ በመፈለግ ነው።

3. ኃጢአቱን ከእግዚአብሔር መደበቅ የሚችል ሰው አለ?

ሀ- የለም።

ለ- ኃጢአቱን ከእግዚአብሔር መደበቅ የሚችል ማንም የለም።

4. አዳምና ሔዋን ከቅጠል የሠሩት ልብስ በእግዚአብሔአር ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በእርሱ ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነው።

5. እኛ በምንለብሳቸው ልብሶች በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት እንችላለን።

ሀ- አንችልም።

6. በምንሠራቸው ሥራዎች በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት እንችላለን።

ሀ- አንችልም።

7. አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን እንዲያገኙ ማድረግ የሚችለው ማን ብቻ ነው?

ሀ- እግዚአብሔር።

8. እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ልብስ ለመሥራት እንስሳን የገደለው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለማስተማር ስለፈለገ ነው።

9. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን እያስተማራቸው የነበረው ምንድን ነው?

ሀ- አለመታዘዝ ሞትን እንደሚያስከትል፤

ለ- ኃጢአት ሞትን እንደሚያስከትል፤

ሐ- የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን።

10. እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ልብስ የሠራላቸው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ስለ ወደደ ነው።

11. አዳምና ሔዋን ይህን ልብስ ራሳቸው ወስደው እንዲለብሱ እግዚአብሔር ያልፈቀደው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር እርሱ ብቻ የሰዎችን ኃጢአት መሸፈን እንደሚችል ለአዳምና ሔዋን እያስተማራቸው ነበር።

ለ- እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ የሚከተሉትን እንደማይቀበል ለአዳምና ሔዋን እያስተማራቸው ነበር።

12. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ወደ ዔድን የአትክልት ስፍራ እንዳይመለሱ ምን አደረገ?

ሀ- እግዚአብሔር ኪሩቤል የተባሉትን መላእክትና የምትገለባበጥ ሠይፍ በዔድን የአትክልት ስፍራ መግቢያ ላይ አኖረ።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ካስወጣቸው በኋላ የሆነው ነገር ምንድን ነው?

## ዘፍጥረት 4፡1

1- አዳም ሚስቱን ሔዋንን ተገናኛት፤ እርሷም ፀንሳ ቃየንን ወለደች፤ «በእግዚአብሔር ርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ» አለች።

- አዳምና ሔዋን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ከተባረሩ በኋላ ሔዋን ልጅ ወለደች።

- ሔዋን የመጀመሪያ ልጇን ቃየን አለችው።

- ሔዋን «በእግዚአብሔር እርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ» ያለችው ለምንድን ነው?

- ሕይወት የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ ስላወቀች ነው።

- ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ማን ነው?
- እግዚአብሔር።

- ለሁሉም ሰው ሕይወት የሚሰጠው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ለአንተም ሕይወት የሰጠህ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

## ዘፍጥረት 4፡2

2- ደግሞም ሔዋን ወንድሙን አቤልን ወለደች።

- በኋላ ሔዋን ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደች።

- ሔዋን ሁለተኛ ልጇን አቤል አለችው።

- ቃየንና አቤል የተወለዱት የት ነበር?

- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ።

- ቃየንና አቤል ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ የተወለዱት ለምንድን ነው?

- አባታቸው አዳምና እናታቸው ሔዋን ኃጢአት ስለሠሩና እግዘብሔርን ስላልታዘዙ እግዚአብሔር ከዔድን የአትክልት ስፍራ ስላስወጣቸው ነው።

- አዳምና ሔዋን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ተባርረው ስለ ነበረ ልጆቻቸው የተወለዱት ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ነበር።

- አዳምና ሔዋን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ይኖሩ ስለነበረ ልጆቻቸውም ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ተወለዱ።

- ሁለት ምሳሌዎች ልንገራችሁ፡-

- ወላጆቻችሁ ጥቁሮች ቢሆኑ እናንተም ጥቁሮች ሆናችሁ ነው የምትወለዱት?
- አዎን

- ወላጆቻችሁ ነጮች ቢሆኑ እናንተም ነጮች ሆናችሁ ነው የምትወለዱት?
- አዎን

- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ስላስወጣቸው ቃየንና አቤልም ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ተወለዱ።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከዔድን የአትክልት ስፍራ ስላስወጣቸው ሰዎች ሁሉ የተወለዱት የት ነው?

- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ።
- ቃየንና አቤል የተወለዱት ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ነው።

- ሁሉም ሰው የተወለደው ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ነው።

- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ሕመም አለ።
- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ጥላቻ አለ።

- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ኃጢአት አለ።
- ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ሞት አለ።

- ሁሉም ሰው የተወለደው ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ ነው።

- ሁሉም ሰው የተወለደው ሕመም ባለበት ዓለም ነው።
- ሁሉም ሰው የተወለደው ጥላቻ ባለበት ዓለም ነው።

- ሁሉም ሰው የተወለደው ኃጢአት ባለበት ዓለም ነው።
- ሁሉም ሰው የተወለደው ሞት ባለበት ዓለም ነው።

- ሁሉም ሰው የተወለደው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ነው።

- ሁሉም ሰው የተወለደው የሰይጣን ባሪያ ሆኖ ነው።
- ሁሉም ሰው የተወለደው የሰይጣን አትገዢ ሆኖ ነው።

- ሁሉም ሰው የሰይጣን ተገዢ ሆኖ የተወለደው ለምንድን ነው?

- አባታችን አዳም ለእግዚአብሔር ስላልታዘዘና ኃጢአት ስለ ሠራ ነው።

- አባታችን አዳም ሰይጣንን ስለታዘዘ ነው።

- ሌላ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- የእናንተን ጐሳ ሊያጠፉ የሚፈልግ ጠላት የሆነ ጐሳ አለ እንበል።

- አንድ ቀን ከእናንተ ጐሳ የሆነ አንድ ሰው ወደ ጠላት ጎሳ ሄዶ ከእነርሱ ጋር ቢኖር እነርሱን ቢመስል ከልጃገረዶቻቸውም አንዷን ቢያገባ፣

- ልጆች ቢወልዱ እነዚህ ልጆች ማንን ይመስላሉ?
- የጠላትን ጐሳ።

- አባታችንን አዳም ሰይጣንን ስለታዘዘና የሰይጣን ባሪያ ስለሆነ ሁሉም ሰው የተወለደው የሰይጣን ባሪያ ሆኖ ነው፥

- አባታችን አዳም ሰይጣንን ስለታዘዘና ሰይጣን ገዢው ስለሆነ ሁሉም ሰው የተወለደው በሰይጣን ግዛት ውስጥ ሆኖ ነው።

- አንድ ቀን ቃየን እና አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ።

ዘፍጥረት 4፡3

3- በአንድ ወቅት፣ ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ።

- ቃየን ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት ምን ነበር?

- ቃየን ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት እህል ነበር።

- አቤል ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት ምን ነበረ?

ዘፍጥረት 4፡4

4- አቤል መጀመሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል ስባቸውን መሥዋዕት አድርጐ አቀረበ።

- አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው በግ ነበር።

- ቃየንና አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀረቡት ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤል ወደ እርሱ ለመቅረብ መሥዋዕት ማቅረብ እንዳለባቸው ስለ ነገራቸው ነው።

- ቃየንና አቤል በራሳቸው መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችሉም ነበር።

- ቃየንና አቤል በራሳቸው መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የማይችሉት ለምንድን ነው?

- በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለ ሠሩና ከእግዚአብሔር ስለ ተለዩ።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ስለሚጠላና ሁሉንም ኃጢአት በሞት ስለሚቀጣ።

- ቃየንና አቤል ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ስለማይችሉ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲቀርቡ መንገድን አዘጋጀላቸው።

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤል ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ያዘጋጀላቸው መንገድ ምን ነበር?

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤል በግ እንዲሠዉለት ጠየቃቸው።

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤል በግ እንዲሠዉለት ለምን ጠየቃቸው?

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤልን ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤልን ሊያስተምራቸው የፈለገው ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር የፈለገው ቃየንና አቤል የበጉን ደም ተመልክተው ኃጢአት ሞትን እንደሚያስከትል እንዲያውቁ ነው።

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤል የበጉን ደም ተመልክተው የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን እንዲያውቁ።

- የበጉ ደም ቃየንና አቤልን ሊያድናቸው ችሏል?
- አልቻለም።

- የበጉ ደም ቃየንና አቤልን ሊያድናቸው ያልቻለው ለምንድን ነው?

- በጉ ኃጢአት ስላልሠራ።
- ኃጢአትን የሠሩት ቃየንና አቤል ብቻ ስለሆኑ።

- ለሰዎች ኃጢአት የእንስሳት ደም ክፍያ ሊሆን ስለማይችል።

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤልን ማዳን የሚችለው እርሱ ብቻ መሆኑን ለእነርሱ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ።

- እግዚአብሔር ቃየንና አቤል ወደ እርሱ መቅረብ የሚችሉት በእርሱ በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ መሆኑን ለእነርሱ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ።

- እግዚአብሔር ስለ አቤልና ስለ መሥዋዕቱ ምን አሰበ?

ዘፍጥረት 4፡4ለ

4- እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ።

- እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን የተቀበለው ለምንድን ነው?

- አቤል እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ።

- አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በግ ስላቀረበ።

- አቤል በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ወደ እግዚአብሔር ስለ ቀረበ።

- አቤል ስለ ራሱ ምን ያውቅ ነበር?

- አቤል በኃጢአት መወለዱን ያውቅ ነበር።
- አቤል ኃጢአቱ በሞት መቀጣት እንደሚገባው ያውቅ ነበር።

- አቤል ስለ እግዚአብሔር ምን ያውቅ ነበር?

- አቤል እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ያውቅ ነበር።

- አቤል እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ነበር።

- አቤል ከኃጢአቱ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቅ ነበር።

- አቤል ደግሞ እርሱን ከኃጢአት ለማዳን አዳኙን እንደሚልክለት እግዚአብሔርን ያምን ነበር።

- ስለዚህ አቤል እግዚአብሔርን ታዘዘና የበግ መሥዋዕትም አቀረበለት።

- አቤል እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ።

- አቤል በእግዚአብሔር መንገድ ወደ እርሱ ስለ ቀረበ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ።

- እግዚአብሔር ስለ ቃየንና ስለ መሥዋዕቱ ምን አሰበ?

ዘፍጥረት 4፡5

5- በቃየንና በመሥዋዕቱ ግን እግዚአብሔር አልተደሰተም፤ ስለዚህ ቃየን ክፉኛ ተናደደ፤ ፊቱም ጠቆረ።

- እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር እህል ስለማይወድ ነውን?
- አይደለም።

- እህልን የፈጠረው እግዚአብሔር ራሱ ነው።

- ታዲያ እግዚአብሔር ቃየንንና መሥዋዕቱን ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

- ቃየን ለእግዚአብሔር ስላልታዘዘ።

- ቃየን ለእግዚአብሔር የበግ መሥዋዕት ስላላቀረበ።

- ቃየን በእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን በራሱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ስለ ፈለገ።

- ቃየን ስለ ራሱ ምን አሳብ ነበረው?

- ቃየን በኃጢአት መወለዱን አላሰበም።
- ቃየን ለኃጢአቱ የሚገባው ቅጣት ሞት እንደሆነ አላሰበም።

- ቃየን ስለ እግዚአብሔር ምን አሳብ ነበረው?

- እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን አላሰበም።

- ቃየን እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት በሞት እንደሚቀጣ አላሰበም።

- ቃየን እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል አላሰበም።

- ቃየን ደግሞ ከኃጢአቱ የሚያድነው አዳኝ እንደሚያስፈልገው አላሰበም።
- ቃየን አዳኙ መጥቶ ከኃጢአቱ እንዲያድነው አልፈለገም።

- ቃየን እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት አልተቀበለም።

- ቃየን በእግዚአብሔር መንገድ ወደ እርሱ ስላልቀረበ እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት አልተቀበለም።

- አዳምና ሔዋን የሠሩትን የቅጠል ልብስ በእግዚአብሔር ፊት ለምን ተቀባይነት እንዳላገኘ ታስታውሳላችሁ?

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነበር።

- እግዚአብሔር ቃየንም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችል ሊያሳውቀው ፈለገ።

- እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ባልተቀበለው ጊዜ ቃየንን ምን አለው?

ዘፍጥረት 4፥6-7

6- እግዚአብሔር አምላክም ቃየንን እንዲህ አለው።
«ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ?
7- መልካም ብታደርግ ተቀባይነትን አታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን፣ ኃጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸንፍህ ትፈልጋለች። አንተ ግን ተቆጣጠራት።»

- እግዚአብሔር የቃየንን መሥዋዕት ከተወ በኋላ ቃየንን ያነጋገረው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ቃየንን ስለሚወድደው።

- እግዚአብሔር ቃየን ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ስለ ፈለገ።

- እግዚአብሔር ቃየን በራሱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደማይችል እንዲያውቅ ስለ ፈለገ።

- እግዚአብሔር ቃየን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚችለው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ መሆኑን እንዲያውቅ ስለ ፈለገ።

- እግዚአብሔር ቃየን ወደ ዘላለሙ የእሳት ባሕር እንዳይገባ ሊረዳው ስለፈለገ።

- ቃየን እግዚአብሔርን ታዘዘው?

ዘፍጥረት 4፡8

8- ቃየንም ወንድሙን አቤልን፣ እስቲ ና፤ ወደ መስኩ እንውጣ አለው፤ በመስኩም ሳሉ፣ ቃየን ወንድሙን አቤልን አጠቃው፤ ገደለውም።»

- ቃየን ለእግዚአብሔር ታዘዘ?
- አልታዘዘም።

- ቃየን ለማን ነው የታዘዘው?
- ቃየን ለሰይጣን ነው የታዘዘው።

- ቃየን ምን አደረገ?
- ቃየን ተቆጣ፤ ወንድሙን አቤልን ገደለው።

- ሰይጣን አዳምና ሔዋን እንዲሞቱ ፈለገ።
- ሰይጣን ቃየን አቤልን እንዲገድለው ፈለገ።

- ሰይጣን ሁሉንም ሰዎች ይጠላል።

- ሰይጣን ሁሉም ሰዎች እንዲሞቱ ይፈልጋል።
- ሰይጣን ሁሉንም ሰዎች መግደል ይፈልጋል።

- ሰይጣን ቃየን ወንድሙን አቤልን እንዲገድል ነገረው ቃየንም ሰይጣንን ታዘዘው።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣንን እንደታዘዙት ሁሉ ቃየንም ሰይጣንን ታዘዘው።

- ቃየን ያደረገውን እግዚአብሔር አይቶአል?

- አዎን አይቷል።

- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያያል ሁሉንም ነገር ያውቃል።

- እግዚአብሔር ቃየን ወንድሙን አቤልን ከገደለ በኋላ ለቃየን ምን አለው?

ዘፍጥረት 4፡9

9- ከዚያም እግዚአብሔር ቃየንን፣ «ወንድምህ አቤል የት ነው?» አለው። ቃየንም፣ «አላውቅም፤ እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?» ሲል መለሰ።

- እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ቃየን የጠየቀው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ቃየን ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ስለ ፈለገ ነበር።

- እግዚአብሔር ቃየን እግዚአብሔርን ያለመታዘዙን እንዲያምን ፈለገ።

- እግዚአብሔር ቃየን ሰይጣንን መታዘዙን እንዲያምን ፈለገ።

- እግዚአብሔር ቃየንን ሌላ ምን አለው?

ዘፍጥረት 4፡10-12

10- እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ «ምንድን ነው ያደረግኸው? ስማ! የወንድምህ ደም ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል።

11- እንግዲህ የተረገምህ ነህ፤ የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፏን ከከፈተችው መሬት ትሰደዳለህ።

12- ብታርሳትም ፍሬዋን አትለግስህም፤ በምድር ላይ ኰብላይና ተንከራታች ትሆናለህ፡»

- እግዚአብሔር የቃየንን ኃጢአት ቀጥቷል?
- አዎን ቀጥቷል።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት ይቀጣል።

- እግዚአብሔር የማይቀጣው አንድም ኃጢአት የለም።

- የቃየን ኃጢአት የተቀጣው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔር ቃየንን ረገመው።

- እንዲሁም ቃየን መሬትን አርሶ በቂ ምርት አያገኝም።

- እንዲሁም ደግሞ ቃየን በምድር ላይ ዕረፍት ያጣ ተንከራታች ይሆናል።

- ቃየን ሰይጣንን እንጂ እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ እግዚአብሔር ቃየንን አባረረው።

ዘፍጥረት 4፡16

16- ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ፣ ከዔድን በስተምሥራቅ በምትገኝ ኖድ በተባለች ምድር ተቀመጠ።

- ቃየን እግዚአብሔርን ማድመጥ አልፈለገም፣

- ስለዚህ እግዚአብሔር ቃየንን አባረረው።

- ቃየን ኃጢአቱንም ለመናዘዝ አልፈለገም።

- ስለዚህ እግዚአብሔር ቃየንን አባረረው።

- በኋላም ቃየን በሞተበት ጊዜ ወደ ዘላለሙ ቅጣት ሄደ።

- እግዚአብሔርን አለመታዘዝ እጅግ ሞኝነት ነው።

- ንስሐ አለመግባትና ኃጢአትን አለመናዘዝ እጅግ ሞኝነት ነው።

- እንደ ቃየን አትሁኑ።

- ቃየን በኃጢአት መወለዱን ለማሰብ አልፈለገም።

- ቃየን ኃጢአቱ በሞት መቀጣት እንዳለበት ማሰብ አልፈለገም።

- ቃየን የእግዚአብሔርን መንገድ አልተከተለም።

- ቃየን የራሱን መንገድ ስለ ተከተለ ወደ ዘላለሙ ቅጣት ሄደ።